DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

# የኢንተርኔት የመገኛ ምንጮች፣ ለቤተሰቦች

**የኢንተርኔት ኢሴንሻልስ (Internet Essentials)**

የኮምካስት ኢንተርኔት ኢሴንሻልስ (Internet Essentials (IE) ፕሮግራም፣ በኮሮናቫይረስ (COVID-19) ምክንያት የደረሰን የትምህርት ቤት መዘጋቶች ጋር በተያያዘ ምላሽ ለመስጠት፣ የተወሰኑ መስፈርቶችን ለሚያሟሉ ቤተሰቦች፣ የሁለት ወር ነፃ የኢንተርኔት አገልግሎት ይሰጣል።

የሁለት ወር ነፃ አገልግሎት የሚሰጠውን ተጠቃሚ ለመሆን ፈጣኑ መንገድ፣ በስማትፎን (smartphone)፣ ታብሌት (tablet)፣ ወይም ኮምፒውተር ወደ https://www.internetessentials.com/covid19 በመሄድ መመዝገብ (sign up) ማድረግ ነው።

**የኤስፊኒቲ የሕዝብ ሆት ስፖቶች (Xfinity Public Hot Spots)**

ኤክስፊኒቲ (Xfinity) ሁሉንም የሕዝብ ሆትስፖቶቹን፣ የኤክስፊኒቲ ደንበኛ ላልሆኑ (non-Xfinity) ሁሉ ክፍት አድርጓል። በሚሸፍነው ስፍራ (coverage area) ውስጥ ከሆኑ፣ ወደ“xfinitywifi” በዋይፋይ (WiFi)፣ መግባት እና ውሎችና ሁኔታዎቹን (terms and conditions) መቀበልዎን ‘accept’ን መጫን።

ለተጨማሪ መረጃ https://www.xfinity.com/support/articles/open-xfinity-wifi-hotspots ይጎብኙ።

**የቲ-ሞቢል / ሜትሮ ፒሲኤስ ደንበኞች (T-Mobile / Metro PCS Customers)**

ከመጋቢት 4 ቀን 2012 ዓ.ም (March 13, 2020) ጀምሮ፣ ሁሉም የቲ-ሞቢል እና የሜትሮ፤ በቲ-ሞቢል አገልግሎት ከመረጃ ስብስብ ጋር (plans with data) ያላቸው ደንበኞች፣ (ሩሚንግ ‘roaming’ ሳይጨምር) እስከ ግንቦት 5 (May 13) ድረስ ያልተገደበ የስማርትፎን የመረጃ ስብስብ (unlimited smartphone data) ወዲያውኑ ያገኛሉ።

ለተጨማሪ መረጃ፡ https://www.t-mobile.com/support/account/covid-19-updates#heading2 ወይም https://www.metrobyt-mobile.com/ongoing-updates-covid-19#customers ይጎብኙ።

**የOCTO ነፃ የሕዝብ ዋይፋይ (WiFi)**

የዲሲ ቢሮ ዋናው የቴክኖሎጂ ሹም (The DC Office of the Chief Technology Officer (OCTO)፣ የተመቻቸ ከተማ አቀፍ የዋይፋይ (Wi-Fi ) ኢንተርኔት ማግኘት እንዲቻል፣ በእያንዳንዱ ዋርድ ሆት ስፖቶችን (hotspots) አስገብቷል።

በቅርብዎ የሚገኘውን የሕዝብ የዋይፋይ (WiFi) ስፖት ለማግኘት፣ እዚህ https://octo.dc.gov/wifi ይጎብኙ።